# ኢትዮጵያ

ሐምሌ/ነሐሴ 2006 ዓ.ም. 2ኛ ዓመት



ማንያዘዋል ካሳ (ማቴዎስ)
የኢሕአፓ አመራር አባል የነበረና በአገር ውስጥ በጽናት እየታገለ እያለ በህመም በሞት የተለየን


**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**

ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት - በማይዛነፍ የቃል ኪዳን /

//

**ዜና ከተባለ ገፅ 3**

**ምን ይሰማ....... አገር ገፅ 3**

//

**ትላንትና ገፅ 5**

- በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

//

**ነፃ ሀሳብ ገፅ 6**

- የሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ፖለቲካ
- ድልን ያራቁ ዋና ዋና ችግሮች


## የአውሮፓ ህብረት ወያኔን አወገዘ

ለወያኔ አገዛዝ በብዙ መቶ ሚሊዮኖች የገንዘብ እርዳታ በማድረግ የሚታወቀው የአውሮፓ ህብረት፤ የወያኔን የሰብአዊ መብት ረገጣ አስመልክቶ ተቃውሞውን አሰማ፡፡ የአውሮፓ ህብረት ባወጣው በዚሁ የተቃውሞ መግለጫ ፤ በድረ ገጽ ጽሁፍ ሲያቀርቡ የነበሩት ዘጠኙ ጋዜጠኞች ፤ ቀደም ሲል እስር ላይ ያሉትን ጋዜጠኞች እና በቅርቡ የታገቱ የፖለቲካ ሰዎችን ጠቅሶ ፣ የወያኔ ጸረ ሽብር ህግ ተብዬው ተቃውሞን ለማፈን መዋል የለበትም ፤ የፖለቲካ እስረኞችም ቢሆኑ ቤተሰቦቻቸውና ጠበቆቻቸው እንዳይጎበኟቸው መከልከሉም የሰብአዊ መብት ረገጣ ነው ሲል ለስለስ ያለ ተቃውመሞውን አሰምቷል፡፡

ከሰላሳ አምስት ሺ በላይ የፖለቲካ እስረኞችን ካለፍርድ እስር ቤት አጉሮ እያሰቃየ ያለው ወያኔ ግን ይህን ድርጊቱን ጭልጥ አድርጎ ክዷል፡፡ ይሁንና በቅርቡ እንኳን የመን ላይ ተይዞ ለወያኔ ተላልፎ የተሰጠውን አንዳርጋቸው ጽጌን ለማየት የሞከረችው እህቱ ተከልክላ ከሀገር መባረሯ እና የእንግሊዝ ኢምባሲም እንዳይጎበኘው መከልከሉም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ወያኔ ከፍትህ ጋር የተጣላ እና በሕዝብ ላይ ግፍ እየፈጸመ ያለ መሆኑን የአውሮፓ ህብረት አምባሳደሮች ጠንቅቀው የሚያውቁ ቢሆንም ፤ እስከ አሁን አንዳችም እርምጃ አለመውሰዳቸው የሚታወቅ ሲሆን ፤ አሁንም ተቃውሟቸው በኢትዮጵያውያን ይታመን ዘንደ ለወያኔ የሚያደርጉትን የገንዘብ እርዳታ ማቆም አለባቸው ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

## ወያኔ ፣ ለቢልጌት ዲግሪ ሰጠው

የማይክሮ ሶፍት ባለቤትና ቢሊዮነሩ ቢልጌት ፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ማግኘቱን እና ይህንኑንም ተከትሎ ወያኔ በሚቆጣጠራቸው ዜና ማሰረጫዎች ሲደሰኩር መሰንበቱን ከዛው ከአዲስ አበባ የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በፊት ይኸው ቢልጌት ፣ አገሪቱ በወያኔ አስተዳደር ማደጓን ፤ በተለይም በጤና ጥበቃ መመንደጓን አስመልክቶ በእጅጉ ከእውነት የራቀ ምስክርነቱን ከመስጠቱም በተጨማሪ ፤ ዘረኛው መለስ ዜናዊ በሞተ ጊዜ ፤ ለዚሁ ነፍሰ ገዳይ ግለሰብ ውዳሴ ሲያሰማ እነደነበር የሚታወስ ሲሆን ፤ ወያኔም ስለቢልጌት በሚዲያዎቹ ሲደሰኩር መሰንበቱ ፤ ይህ ግለሰብ ወያኔን እየረዳና እየታደገ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ተብሏል፡፡

ይህንኑ በተመለከተ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ለግለሰቡ ግልጽ ደብዳቤ የጻፈለት ሲሆን ፤ በዚሁ መንገድ ድምጻቸውን በማሰማት እና ተቃውሟቸውን በመላክ ከድረጊቱ እንዲቆጠብ ሊየሳስቡት ይችሉ የነበሩ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ፣ በተለይም በአሜሪካ ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያዉያን ጸጥታን በመምረጣቸው እንጂ ፤ ቢልጌት የሀብታም እብሪት ቢጠናወተውም ለወያኔ የሚያደርገውን ድጋፍ መለስ ብሎ ሊመረምር ይገደድ ነበር ተብሷል፡፡ ለወያኔ አጭበርባሪ ዘመቻ ሰለባ እየሆኑ ወያኔን የሚረዱትን መንግስታትም ሆኑ ግለሰቦችን በተቃውሞ ማዋከቡ የትግላችን አንዱ ተግባር መሆን አለበት ሲሉ አንዳንድ የተቃዎሚ ድረጅት መሪዎች አሳስበዋል፡፡

## የወያኔ ሽኩቻ ቀጥሏል

ቁጥር አንድ የኢትዮጵያ ጠላት የነበረው መለስ ዜናዊ ፤ በካንሰር በሽታ ከሞተ ጀምሮ አፍኖ ይዞት የነበረው የውስጥ ቅራኔ ከቁጥጥር ውጭ መውጣቱ የአደባባይ ሚስጢር መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ፤ አሁን ደግሞ የአማራው ድርጅት መሪ ነኝ ባዩ ኤርትራዊው በረከት ስምኦን በህመም እየማቀቀ ነው በሚባልበት በዚህ ወቅት ፤ የእርስ በርስ ሽኩቻው የበለጠ መባባሱን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ፡፡

በመቀሌ እና የአዲስ አበባው ቡድን ተብሎ የተከፋፈለው ወያኔ ፤ እስካሁን የአዲስ አበባው የእነደብረ ጺዮን ቡድን የበላይነትን ተቆጣጥሮ መቀጠሉ ይነገራል፡፡ከዚህ ተያይዞም አውራጃዊነት መጧጧፉ ሲታይ ፤ በውልደት ኤርትራዊ የሆኑት (እነ ቴድሮስ አድህኖምን ጨምሮ) ደግሞ ከትግራይ ተወላጆች ጋር ግብ ግብ ላይ መሆናቸውም የሚደበቅ አልሆነም፡፡ ስበሐት ነጋ ተሳስቷል ፤ አሰብ የኢትዮጵያ ነው ፤ የሚሉ ብቅ ብቅ ማለታቸውና መድረክ ማግኘታቸው ፤ በኢሳያስ ላይ ወረራ እናድርግ የሚሉ አፍ ሞልተው መናገር መቻላቸው የልዩነቱን ጥልቀት ገላጭ ነው የሚሉ አሉ፡፡

በቀጣይ ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ከስልጣን እነዲወገድ ምክንያት ይሆናሉ ከሚባሉ አበየት ክስተቶች ፣ በጦሩ ውስጥ ያለው ውዝግብ እና መከፋፈል ፤ በየቦታው ዜጎች እያደረጉ ያሉት ጠንካራ ተቃውሞ ፤ በራሱ በወያኔ ውስጥ ያለው ዋልጌነትና ሙስና ፤ የሰብአዊ መብት ረገጣው ተባብሶ መቀጠሉ ፤

ወደ ገጽ 4 ዞሯል....






የኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰልፍ በዋሽንግተን ዲሲ August 4, 2014



የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

EPRP.COM
ASSIMBA.ORG
DEBTERAW.COM
ETHIOLION.COM
ወዘተ.

- FACE BOOK (ethiopianewspape

# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል**
**የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ**



አድራሻ፡ 5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com


## ርዕሰ አንቀጽ

## ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት - በማይዛነፍ የቃል ኪዳን /

ለግፉአኑ ሕዝብ መመኪያ ፤ ለእኩልነትና ለሥልጣን ባለቤትነት እስከዛሬ ድረስ ለሚደረገዉ ትግልም አለኝታ ክንድ ሊሆን ከተማሪዎች እንቅስቃሴ አብራክ በ፩፱፻፷፬ ዓ.ም የተወለደዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ) የአርባ ሁለተኛዉን የልደት በዓሉን ሻማዎች አብርቷል ። በነዚህ ዘመናት በሀገራችን ዉስጥ ከተከሰቱት ሶስት ተከታታይ ጸረ ሕዝብ አገዛዞች ጋር የተካሄደዉንና እስከዛሬም በመደረግ ላይ ያለዉን ትግል ከፊተኛዉ ረድፍ ሆኖ በመምራት ላይ ይገኛል ።

ኢሕአፓ ፤ የዕድሜ አንጋፋነቱን ያህል፤ በአጠቃላዩ የሀገራችን የፖለቲካ ባህል ዉስጥ ዘመናዊ ድርጅታዊ አሠራርን በፋና ወጊነት በማስተዋወቅ ካደረገዉ የላቀ አበርክቶ ወዲያ የየካቲቱን አብዮት ተከትሎ በሕዝብ ንቃተ ሕሊና ረገድ ለታየዉ እመርታ የቸረዉ ድርሻ ታላቅ ነዉ ። የዚያኑ ያህልም ከኢትዮጵያ ሥነ መንግሥታዊ ዐዉድ አጼያዊዉን ሥርዓትና ዘግናኙን አስገባሪ ሥልተምርቱን እስከወዲያኛዉ በማሰናበት ፤ የተመዘገበዉ ስኬትና ድል ኢሕአፓ ገና በለጋ ዕድሜዉ ከሌሎች አብዮታዊ ኃይሎች ጋር በመሆን ያደረገዉ ብርቱ እንቅስቃሴ ዉጤት መሆኑ ግልጽ ነዉ ።

ንጉሣዊዉን ሥርዓት ተከተዉ ከሥልጣኑ ማማ ላይ የተደላደሉትን የደርግና የወያኔ አገዛዞች ገና ከጅማሮአቸዉ ፋሺስታዊና ጸረ ኢትዮጵያ ባህርያቸዉን በመተንተን ከማጋለጥ አንስቶ የሕዝቡ ቀጥተኛ የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበትን ዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ ደንብ ለመትከል በተደረገዉና በመደረግ ላይ በሚገኘዉ መልከ ብዙ ትንቅንቅ ፤ ኢሕአፓ ከሰላማዊ መድረክ እስከ ታጥቆ ትግል ድረስ በየፈርጁ የተጫወተዉ ወደር የለሽ ሚና በታሪክ ዉስጥ ምንጊዜም ሲያንጸባርቅ ይኖራል ።

እርግጥ ነዉ ትንቅንቁ መንግሥታዊ ሥልጣንን በእጃቸዉ ካስገቡ ተከታታይ ጨካኝ አገዛዞችና በርዳታ ስም እየተፈራረቁ ከጎናቸዉ ከሚሰለፉ ኃያላን መንግሥታትም ጋር የሚደረግ በመሆኑ ሳቢያ ከጠላት ወገን በድርጅቱ ላይ የተሰነዘረዉን በትር ክብደትና ያደረሰዉንም ጉዳት አሳንሶ ማየት አይቻልም ። ይህም በበኩሉ ትግሉን ረዢም ፤መራርና ዉስብስብ ሊያደርገዉ ችሏል ። ይህም ሁሉ ሆኖ ግና ኢሕአፓ ለሀገርና ለወገን ያለዉ ወገናዊነት በደም የታተመ መሆኑን በአባላቱና በደጋፊ ጓዶቹ መሥዋዕት ደጋግሞ ከማስረገጥ አልተገታም ። ኢሕአፓ ፤ የሀገርን አንድነትና ሉአላዊ ክብር ፤ የሕዝቡን እኩልነትና የሥልጣን ባለቤት ጉዳይ ምድር ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢል ከቶ ለድርድር የማያቀርብ መሆኑን እንኳንስ ሕዝባችን ጠላቶቹም አሳምረዉ ያዉቁታል ።

ኢሕአፓ በክብር በተገባ ቃልኪዳን ራሱን ለሕዝብ የሰጠ ድርጅት ነዉ ። በሥሩ ሆነዉ ሲታገሉ በወደቁ ኢትዮጵያዉያን ክቡር መሥዋዕት ደምቆ ፤ የተመሠረተበትን አርባ ሁለተኛ ዓመት በሚያከብርበት በዚህ የታሪክ አጋጣሚም የድርጅቱ ባለቤት የሆነዉ ሕዝብ ገና ነጻ እንዳልወጣና ኢሕአፓም የታገለላቸዉ ዓላማዎች ከግብ እንዳልደረሱ ጠንቅቆ ይረዳል ። በተለይ በዛሬዉ እዉነታ ትግሉ እጅግ ከለየለት ጸረ ኢትዮጵያና ከፋፋይ ከሆነ ኃይል ጋር የሚደረግና የሀገራችን ህልዉናም አስፈሪ አደጋ የተጋረጠበት የመሆኑን ያህል ወያኔያዊዉን አገዛዝ በአንድነት ቆሞ ሊመክት ይገባዉ የነበረዉ ተቃዋሚም ከክፍፍሉ አዙሪት ባልራቀ ግብዝነት እንደሚዳክር ይገነዘባል ። ባለንበትም ወቅት ከኢትዮጵያዊነትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትና እኩልነት በላይ በጋራ ቆመዉ በጽናት ሊዋጉለት የሚገባ ዓላማ አለመኖሩን ኢሕአፓ በርግጠኛነት ያምናል ።

በመሆኑም በድርጅቱ ዙርያ የተሰለፍን ሁሉ ፤ ከንጹህ የሕዝብ ፍቅርና ከታላቅ ዓላማ ከሰረጸ ጥብቅ እምነት በሚቀዳ ወኔና ጽናት ቆመን ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ለአገራቸዉ እኩል ባለቤት የሚሆኑበት የፍትህ ዘመን እስከሚጠባ ፤ ለሕዝባዊዉ ትግል አቸናፊነት በቁርጠኛነት ቆመን ለመታገል የገባነዉን ቃልኪዳን እናድሳለን ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል/
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

## መልእክት ከአንባብያን

እናት ኢትዮጵያ፤ በጣም ደስ ይበልሽ
42 ዓመቱን፤ አከበረልሽ
ጊዜ የማይሽረው፤ ኢሕአፓው ልጅሽ።
ኢሕአፓ አንድ ነው፤ አንድም ለኢትዮጵያ
እምነቱም አንድ ነው፤ ነፃ ኢትዮጵያ
ራዕዩም አንድ ነው፤ ድልን ለኢትዮጵያ።
ለታጋይ ድርጅት፤ የሚሆን አርአያ
ለሐቀኛ ፓርቲዎች፤ የሚሆነው መኩሪያ
ለቆራጥ ልጆችሽ፤ ለሆነው መለያ
አንድዩው ኢሕአፓ፤ ለእናት ኢትዮጵያ።

ከጎላ ምንጭ

## እንቆሥቁሥ ! ይጫጫሥ !
ከዓሣዬ

እንደ ድፎ ዳቦ ኣገር ሥትቆረስ
ንብረቷ ተሟጦ ባዕድ ኣገር ሲፈሥ
የዜጋን ሃብት ንብረት በእሣት እያጋየው በዶዘሩ ሲያፈርሥ፣
በጠባብ ወያኔ በማፍያው ዘረኛ
በገዛ ኣገራችን ከሆንን ሥደተኛ !
ከእንግዲህ ምን ቀረን?!
እንቆሥቁሥ ይጫጫሥ !
እናቃጥለው ይንደድ !
ዳር ቆመን ከማየት ኣገር ሥትዋረድ !

**እነሱ ሲጠግቡ እኛ ግን ተርበን**
ዘረኞች ሲከብሩ ደሃ ለማኝ ሆነን
ተንቆ ክብራችን በገዛ ኣገራችን
ጉርሻ በቀን ሲሆን የኛ ዕጣ ፋንታችን ፡
እኛ እየተገፉን ሥንሆን ኣገር ኣልባ
ዘረኛው ማፍያ ተብሎ ምርጥ ዜጋ
መሆን ከተገደድን ላገራችን ባዳ

ለሕዝቡም እንግዳ ከእንግዲህ ምን ቀረን? !
ለወያኔው ማፍያ ሠግደን በማጎብደድ

ዳር ይዘን ከምናዝን ኣገር ሥትዋረድ !

ያገር ዕዳ ኣለብን !
እንቆሥቁሠውና እሣቱ ተቀጣጥሎ ዕቶን ሆኖ
ይንደድ !

በዘር በሃይማኖት ጣልቃ እየገባ
በሌሊት በር ሰብሮ መድረሻ ካሣጣ
የዓይን ቀለምህ ብሎ፡
ሥየል ከዳረገን በነጋ በጠባ

ከዚህ በላይ በደል ሌላ ምን ሊመጣ?
በፍርሃት እጅ ሰጥተን ይበልጥ ሣንዋረድ

ክብሪቱ ይጫርና !

ከመሃል ኣሥገብተን ! እናቃጥለው ይንደድ !
የኣያት ቅድመ ኣያቶች ኣደራው ኣለብን ! ላገር ልንታደግ !

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! ሞት ለወያኔ**

# ዜና ከተባለ

**መሰተዋት ከድሬ**

የወያኒ አረመኔዎች አንዋር መስጊድ በሀይል ገብተው ሙስሊም ዚጎችን ደበደቡ፤አፈሱ፤ ባለጉ፣
የአንዳርጋቸው ጽጌ ጉዳይ ውዝግቦችን አባባሰ፣
ወያኒ የሕዝብ ንብረት ዘረፋውን ገፋበት፣
አሚሪካ የአፍሪካ አምባገነኖችን ማቀፍ ቀጠለች፣
የወያኔ መብት ረገጣ ልክ አጣ፣

ይህ ሁሉ ዜና የሚባል ላይሆን ይችላል ። ሰውየው ውሻውን ነከሰ ዓይነት አይደለም ። ሆኖም ዜና ስለተባለ መዘርዘር ያለበት ነውና መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ። ወያኔ የሙስሊም ዜጎችን ቀጣይ ትግል ሊያደባይ ያልሞከረው ሸር፤ተንኮልና ድርጊትም የለም ። አያለ ሙስሊም ዚጎችና የሀይማኖት መሪዎች ታግተዋል፤ስየል ተቀብለዋል ። ወያኔም በአንዋር መስጊዱ ጥቃቱ ላይ ዜጎችን ወደ ሳውዲ አረቢያ ሂዱ-ተመለሱ እያለ በጻያፉ መለፈፉም ተደምጧል ። ሁናቴው ነጋ ጠባ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ መሆኑ ያስቆጣቸው ሙስሊሞች ምናልባትም የትግሉን ስልት መቀየሩ አስፈላጊ ይሆናል ወደሚል መደምደሚያ እንዲጓዙ እየገፋፉቸው ነው ። ይህም በአንድ ጎኑ ለወያኔ ሊያመች የሚችል በመሆኑ የሚጠይቀው ጥንቃቂ ግልጽ መሆን ያለበት ነው። ያለፈውና አሁንም ያለው የህቡዕ ትግል ተመክሮ ብዙ መልዕክትና ትምህርት አለው። የአንዳርጋቸው ጽጌ መታሰር በዚህም መልክ ሊጠቀስ የሚችል ነው ።

ባዕዳን ለ 23 ዓመታት ወያኔን ሲረዱና ሲደግፉ መቆየታቸው የታወቀ ሲሆን እንግሊዝ በተለይ ባላት ታሪካዊ ጸረ ኢትዮጵያ አቅዋም መሰረት ገንጣዮችን ስትረዳና ወያኔንም ስትደግፍ ቆይታለች ። የወያኔን የአፈና ተቋም በማጠናከር ረገድ እንግሊዝ ሚናዋ ከፍተኛ እንድነበርና አሁንም እንደሆነ የሚታወቅ ነው ። በመሆኑም በአንዳርጋቸው ጽጌ መጠለፍና ለወያኔ መሰጠት የስለላ ተቋሞቿ እጅ አለበት የተባለውን በቀላሉ ማስተባብል የሚቻል አልሆነም ። እንግሊዝ ዜግነት የሰጠችውን አንዳርጋቸው የቅርብ ክትትል ስታረግበት እንደቆየች ተነግሯል ። አንዳርጋቸው በየመን ሲያዝና ለወያኒ ሲሰጥ እንግሊዝ ታውቅ ነበር የሚለው ክስ አነጋጋሪ ነው ። ማነው አንዳርጋቸውን በሰነዓ የመን በዚህ ሰዓት ያልፋል ብሎ ለወያኔ የነገረ? የወያኔ ቁንጮ አመራሮች እናሳግተው ወይስ አያስፈልግም ብለው የተወያዩ መሆናቸው ቀድም ሲል ስለ ጉዞው ማወቃቸውን ገልጿል ። እንዴት ሊሆን ቻለ? መልስ አልባ የሆኑ ጥያቂዎች ጥቂት አይደሉም ። ባንጻሩ ወያኔ ቀስ በቀስ አንዳርጋቸው ተናዘዘ በሚል የሚያቀርበው ቪድዮም አለ ። ጉዳቱ የሚካድ አይደለም ። ድርጅቱ የመረጠው መከላከያ መንገድ ጠቃሚ ነው ወይም ይበልጥ ጎጂ የሚለውን ጥያቄ ታዛቢዎች እንዲመልሱ ትተን በሌላ በኩል ግን አንዳርጋቸው ላይ የደረሰውን በመቃወም በሚደረጉ ሰልፎች ላይ የሚጠበቀውን ያህል ዜጋ አለመገኙትን ሳንጠቅስ የማናልፈው አይደለም ። ይህ እንዳለ ሆኖ አሁንም ቢሆን ስለ መሰል መብት ረገጣ ሲነሳ ከዚህም ከዚያም ስም ጠቀሳው ደርቶ በኢሕአፓ አባላት ላይ የደረሰውን ጠለፋ በሚመለከት (በሱዳን ታግቶ ለወያኔ ከተሰጡት መሃል አዛናው ደምሌ እስከዛሬ ደብዛው እንደጠፋ ነው) ግን ዝምታን የመረጡ አሉ ። መታረም የሚገባው ስህተት ቢባል ተገቢ ነው ። ወያኔ በእገታው አሳቦ በርከታ ዜጎችን እያሰረ መሆኑም እየታየ ያለ ነው ። አፈናው መቀጠሉም ይጠበቃል ። በሀገር ቤት በህጋዊነት ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች የተነፈሱት አለመኖሩም ያለውን ድክመትና ችግር ጠቁሟል ። አንዳርጋቸው ጽጌን በተመለከተ ያሉት ግምጋሚዎች የተለያዩ ቢሆኑም እገታውን መቃውምና እንዲፈታም መጠየቅ ግዴታ ነው ።

አረና ትግራይ የሚባለው የነ ገብሩ አስራት ተቋም ውሎ አድሮ በወያኔ ቁጥጥር ስር መግባቱን ድርጅቱን ለቀቅን የሚሉ መሪዎች (ቡድኑ አባረናቸዋል ይላል ) አጋልጠዋል ። መስራቹ ገብሩ አስራት የቆየ የወያኔ አመራር አባል እንደነበርና በጸረ አማራነቱም ከመልስና ስብሓት የማይተናነስ መሆኑን የሚያውቁት ያረጋግጣሉ። የአረና የዛሬው መሪ ደግሞ- በርሔ-ከመሰረታዊው የወያኔ ዘረኛ አቅዋም ጋር ቅንታትም ጠብ እንደሌለው ይነገራል ። ጉዳዩ የወያኔ ተቃዋሚ በሉን ባዮች ወያኔዎችን ይዘት የሚጠቁም ነው ። ብዙዎቹ ከወያኔ ዘረኝነት ያልተላቀቁና ለተፈጸመው ወንጀልም ቅሬታ የሚያሰሙ አይደሉም ። ከተወልደ እስከ ስዬና ሊሎቾም ጭምር በትግራይ የበላይነት የሚያምኑ ናቸው። ከወያኔነታቸው አልተላቀቁም፤ የወያኔም ምስጢር ምስጢራቸው ነው። ደብዛቸው ስለጠፋው የፖልቲካ አስረኞች (በተለይም የኢሕ አፓ መሪዎችና አባላት) ዛሬም መልሳቸው የምናውቀው የለም የሚል ነው ፡፤ ወያኔ የጎደርና ወሎን መሬት መዝረፉን አያወግዙም። ውሎ አድሮ ያው ናቸው--ወያኔ። ለዚህም ነው ከሕዝብ ጎራ ገባን ሲሉም ያን ወያኔታቸውን ይዘው በመሆኑ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው በልጦ እየተገኘ ያለው።

ወያኔ ትግራይ እንድትለማ መላ ሀግር ይድማ የሚለውን አቅዋሙን ቀጥሎበታል። በቅርቡ በፍቼ በአዲስ ከተማ የህዝብን ንብረት ዘርፎ ወደ ትግራይ ሊያጓጉዝ ሲጥር ሕዝብ ስለተቃወመ በከፈተባቸው ተኩስ ዜጎች ሞተዋል ። ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የሕዝብን ንብረት (ሙብራት ቆጣሪም ሳይቀር) ዘርፎ ወደ ትግራይ መውሰዱ የሚካድ አይደለም ። ትግራይን የመገንባቱ አላማ--አስፈላጊ በሆነበት ትግራይ ለመገንጠል- ሳይቋረጥ እየቀጠለ ነው ። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ቅርስና ንብረት ምህረት አልባ ሆኖ መዝረፍን የግድ ይላል ። ለዚህ ዝርፊያ የቀጥታ ተባባሪ የሆኑ (ከአርከበ በአዲስ አበባ የተዘረፈ 50ሺ ሚትር ካሪ መሬት የተረከበው ሀይሌ ገብረ ስላሴም ሰሞኑን እየተጠቀሰ ነው ) እንዳሉት ሁሉ ተሞኝተው ለወያኔ የሚጠመውን ከሀገር ጥቅም ጋር አዛብተው ሰለባ የሆኑትም በርካታ ናቸው ። የሀገራችንን ንብረትና መሬት ከሚቀራመቱት አንዷ የሆነችው ቻይና ለምሳሌ በኢትዮጵያ ለወያኔ ጉቦ በመስጠት ከሁለት ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ አውጥታለች ሲባል የዚህን አስር ሀያ እጥፍ ግን ለራሷ ማስገባቷም ታውቋል ። ዛሬም ቢሆን በወያኔ ተወናብደው በግድብ ግንባታ ሽፋን ገንዘባቸውን ለጸረ ሕዝቡ ወያኔ የሚገብሩ አሉ ። መቆም ያለበት ስህተት ነው ።

አሜሪካ የአምባገነኖች ደጀን መሆኗ ዚና መባል የሚገባው አይደለም። ኢትዮጵያን በተመለከተ አሚሪካ እንደ መንግስት ያላትና የነበራት አቅዋም የሕዝብ ጠላቶችን መርዳት ማጠናከርና የሕዝብን ትግል ማደናቀፍ ነው ። የቅርቡን ብናነሳ ለወያኒ ለስልጣን መብቃት፤ ለኢርትራ መገንጠል፤ ለግንቦት 97 ምርጫ ውጢት መሰረቅ፤ ለሙት ከተማ አድማ መክሽፍ ወዘተ አሚሪካ ተጠያቂ ናት ። ይህንን ጸረ ሕዝብ አቅዋሟን ደግሞ በመላ አፍሪካም አስፋፍታ የያዘችው ነውና የአፍሪካን አምባገነኖች ወደ አሚሪካ አባማ መጋበዙ ብዙም የሚያስደንቅ መሆን የለበትም ። ይህንንም መቃወም የሚጠበቅ ነው ። ተቃውሞ ግን ለአሜሪካ በሚገባት መንገድ መሆን እንዳለበትም መዘንጋት የሊለበት ነው ። በአባማ ስብሰባ ላይ የሚገኙት አማባገነኖች በጋራ ሚሊዮን በላይ አፍሪካኖችን የጨረሱ፤ መቶው ሺዎችን ያገቱና ለስየል የዳረጉ፤ሀገራቸውን የዘረፉና ያደቀቁ አረመኔዎች ናቸው ። ሀፍረት ለአባማና አሜሪካ!!

## እስቲ ለማንኛውም ችግር የቤት ልጅ የሆነባትን ሀገራችንን በሚመለከት የሚከተሉትን እናጢን---

- ኢሕአፓ ደም ለማፋሰስ ዝግጅት ላይ ነው በማለት ፓርቲውን የሚወነጅል ጽሁፍ በወያኔ ድረገጽ ላይ የወጣ ሲሆን ድርጅቱን ከዚህ በፊት ለማፍረስ ሞክረው ያልተሰካላቸው ክፍሎች ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በእንሰባሰብ መፈክር ዙሪያ የድርጅቱን አባላት ለመከፋፈል አዲስ ከይሲ (ግን የሚክሽፍ ጥረት) መጀመሪያቸውን ማወቅ ተችሏል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ምን ይሰማ……አገር?



**“አንድ ባልዲ ትርፍራፊ ( ምግብ ) ከ15 እስከ 40 ብር ከሆቴሎች ይገዛል ። የሚቸረቸረዉ ደግሞ በሰሃን ከ2 እስከ 5 ብር ነዉ ።”**

(“የትርፍራፊ ትሩፋት” በሚል ርዕስ ሪፖርተር ጋዜጣ በማህበራዊ ዐምዱ ያሰፈረዉ ፤ ጁላይ ፳ ፳፻፲፬)

- **ርዕሱ “የዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ትሩፋት “ በሚል ቢስተካከል ምን ይመስላችኋል ሪፖርተሮች ?**

//

**“የአንዳርጋቸዉ ጽጌ ጉዞ አስቀድሞ እንዴት ታወቀ ?”**

(ጎልጉል የድረ ገጽ ጋዜጣ የተጠቀመበት ንዑስ ርዕስ፤ ጁላይ ፲፩ ፳፻፲፬ )

- **እጅግ ተገቢ ጥያቄ ነዉ ። ለመልሱ ጥያቄዉን ከዬት እንጀምር ?.....ከኤርትራ ?? ወይስ ከራሳችን ጓዳ ?? ...ወይስ.......????.....**

//

**“ኢህአዴግ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ከ 1.3 ሚሊዮን ብር በላይ ሰጠ ።”**

(ሪፖርተር ጋዜጣ በጁን ፳፻፲፬ ዕትሙ እንዳስነበበዉ)

- **ለታማኝ አገልጋይነታቸዉ ደመወዝ መሆኑ ነዉ ። “ ወይም ካልሰበቱ - ወይ ካላሳበቱ ፤ ወይም ካልሰረቱ - ወይ ካላሰረቱ ....ማን ለማን ያቀምሳል ከዚያ ከሱረቱ ? “ ብሏል የልብ አዉቃዉ ጥበበኛ *መንግሥቱ ለማ* በዉስጠ “ቀ” ግጥሙ ።**

//

**“ኤርትራ ለኢትዮጵያ ቁልፍ ተቃዋሚዎች የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት መስጠት ጀመረች ።”**

(ኢትዮጵያን ሪቪዉ ተብሎ የሚጠራዉ የሻቢያ አፈቀላጤ ድረ ገጽ እንዳሰፈረዉ፤ አገስት ፲፫ ፳፻፲፬)

- **“ስቀሽ አታስቂኝ ፤” ነዉ የሚል ዘፋኙ ?/ ....ለነገሩ ፤.ለወዲ አፈወርቂ የቤት ልጆች ፤ አሥመራ የሚታተም የይለፍ ወረቀት ጸረ ሰዉ ፈንጂ የሚጠመድበት መስሎ ቢታያቸዉ ሊያስገርም አይችልም ።**

//

**“ዱሮ ድልድይ ከማፍረስ ጀምሮ ፤ አሁን አገር የሚመራ ሽፍታ ራሱ አሸባሪና ወንበዴ ነዉ ። “መንግሥት” ሳይሆን በግድ በሕዝብ ላይ ራሱን የጫነ “ አገዛዝ” ነዉ ። ይህም አጠራር ሲበዛበት ነዉ ።”**

(ጎልጉል የድረ ገጽ ጋዜጣ በጁላይ ፲፩ ፳፻፲፬ ዕትሙ ያስነበበዉ )

- **ሀሎ ኢሳት/ሬዎች .... አይሰማም ?? ወያኔን የምታቆላምጡበት ቋንቋ እጅ-እጅ ብሎናል ይሏችኋል ።**

ከገጽ 1 የዞረ

ሥርአቱን ቀውስ ውስጥ ሊከቱትና ፍጻሜውን ሊያፋጥኑት ይችላሉ ተብሏል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ጸረ ወያኔው ትግል መፋፋሙ አማራጭ የሌለው ነው የሚሉ ክፍሎች ፤ ሕዝብ የወያኔን ክፍፍል ማባባስና ወያኔን ለማዳከም ብሎም ለማስወግድ መጠቀም መቻል አለበት ሲሉ ያሳስባሉ፡፡

## ገብሩ አስራት ፤ ከዘመዶቹ ተቀላቀለ

በእነ ገብሩ አስራት የሚመራው አረና ትግራይ ፤ የፖለቲካ አቋሙን ከወያኔ ጋር አንድ ማድረጉን የድርጅቱ አባል የነበሩት እና በአሁኑ ወቅት ከድርጅቱ የተወገዱት ወገኖች አስታወቁ፡፡

መምህር ታደለ ቢተውልኝ ፤ መምህር ገብሩ ሳሙኤል ፤ ሸሻይ አዛናው እና አሰግድ ገ/ሥላሴ ፤ የፖለቲካ አቋማቸው ፤ ከነገብሩ አስራት በተቃራኒ በመሆኑ ብቻ ከድርጅቱ መወገዳቸውን አስታወቀው ፤ የድርጅቱ መስራች የሆነው ገብሩ አስራት ዛሬም ቢሆን ከወያኔ ዘረኛ አቋምና መስመር ያልተላቀቀ እና ያልጸዳ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይህ የእነ ገብሩ አስራት ቡድን ለዓመታት በቀውስ ሲታመስ የቆየ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ፤ በመጨረሻም ወያኔ እንቅፋት ናቸው ያላቸውን አስሮ ድርጅቱን ጭፍን ጸረ አማራ ለሆኑት ለነብርሃኑ በርሄ እና ለነገብሩ አስራት ሜዳዉን አመቻችቶ እንደሰጣቸው ይታወቃል፡፡

አረና ትግራይ ፤ የትግራይን ሕዝብ ከወያኔ አላቀው ለሕዝባዊ ትግሉ ሊያሰልፉ ይጥሩ ይሆናል ከሚባሉት ጎራ አለመሆኑን በገሀድ ለማየት ተችሏል የሚሉት ወገኖች ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሻዕቢያ ስር ያለውን ''ደምሀት'' የሚባለውንም ቡድን ሊያሞካሹ እና ሊያዳንቁ የተነሱትም ቢሆን ሀሳዊ መሲሆች ናቸው ተብሏል፡፡

## መሬት የዘረፉ በህግ ይጠየቃሉ

በአዲስ አበባ ከህዝብ እየተነጠቁ ፤ ለወያኔ ደጋፊ ለሆኑ ባለሀብቶች የተሰጠው የመሬት ይዞታዎች ጉዳይ ፤ አወዛጋቢ እና ውስብስብ እየሆነ ከመምጣቱም በሻገር ወደፊት ወያኔን የሚተካውን መንግሥት ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚጠብቀው ጉዳይ ነው ተባለ፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩት አሊ አብዶ እና አርከበ እቁባይ ፤ ከመለስ ጭፍሮች በተለይም ከአዜብ መስፍን ጋር በመተባበር ፤ ሕዝብን ከቤቱ እና ከመሬቱ እያፈናቀሉ ንብረቱን መቸብቸባቸው የታወቀ ሚስጢር ከመሆኑም በላይ ፤ የችኩል ችኩል የቤት ግንባታ ኩባንያዎች (ሪል ኢስቴት) የሚባሉ ድርጅቶችን በማደራጀት ዝርፊያውን አጧጡፈው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ሯጩ ሀይሌ ገ/ሥላሴ ከወያኔ ጋር በጥቅም መተሳሰሩ ድብቅ ካለመሆኑም በላይ ''ሀይሌ እና አለም ሪል ኢስቴት'' የሚል የቤቶች ግንባታ ድርጅት አቋቁሞ ፤ ሀምሳ ሺ ሄክታር መሬት ከአርከበ እቁባይ መረከቡን ተዛቢዎች ዳግም እያነሱ ናቸው፡፡

የሕዝብ መሬት በዘራፊዎች ተወስዶ የማይቀር ከመሆኑም በላይ ይህንን ንብረትም የተቀራመቱት ሁሉ በህግ የሚጠየቁ መሆናቸውን መርሳት የለባቸውም ሲሉ በርካታ ታዛቢዎች በቁጭት ይናገራሉ፡፡

## እንባገነኖች ውግዘት ገጠማቸው


ዋሽንግተን ዲሲ በኢትዮጵያውያኖች ተቃውሞ ስትናጥ ከርማለች፡፡ ወያኔን ጨምሮ ከአርባ በላይ የአፍሪካ ቅል ባለስልጣኖች በአሜሪካ መንግሥት ጋባዥነት "አፍሪካ ሰሚት" በሚል በሽር ገድ ላይ መሆናቸው የወደፊት የአፍሪካ መጻዒ እድል ያሰጋቸው በአስርሺዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ የአፍሪካ ተወላጆች ፤ አምባገነኖችን ለመኮነን በነዚሁ መሪ ተብዬዎች አማካይነት የ አፍሪካን ድንግል መሬት ለመግሰስ የሚያደርጉትን ህገ-ወጥ ተግባር ተወጥራ ከርማለች፡፡

ምንጊዜም ቀዳሚ የሆነችው ኢትዮጵያ ፤ ልጆቿ ባለፈው ሰሞን ፤ ማለትም በኦገስት አራት ቀን ቀጠሮአችን የስብሰባው መክፈቻ በሚደረግበት ስፍራ ከጠዋቱ 7 ሰዓት ጀምሮ በስፍራው በመሰብሰብ ለሰይጣን ምች የሆነውን አረንጓዴ ቀይ ቢጫ ሰንደቃቸውን እያውለበለቡ እና በከፍተኛ ድምጽ እያስተጋቡ ፤ ዘር ሀይማኖት ሳያግዳቸው በአንድ ላይ ኢትዮጵያን አንግሰዋት ውለዋል፡፡

ከጠዋቱ ሰባት ሰዓት እስከ ቀትር በኋላ ድረስ በከፍተኛ ወኔና መንፈስ ፤ በኢትዮጵያዊነት ፍቅር ተቃቅፎ ደምጽ አልባ ለሆኑት ኢትየጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ የማስጠንቀቂያ ደውል ሲያሰሙ ውለዋል፡፡

መነሻቸውን ከሳይንስ አካዳሚ በ 21ኛው ኮኒስቲቲውሽን መንገድ በማድረግ የዓለም ባንክ ድረስ በሺዎች ሆነው በደመቀ ሰልፍ ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ውለዋል፡፡ ይህን ትምህርት በመቅሰም በቀጣይ ቀን ኦገስት 5 ማክሰኞ አመሻሽ ላይ የአፍሪካ አንባገነኖች ፤ በፕሬዚዳንት ኦባማ ጋባዥነት በቤተመንግስቱ የተደረገውን የደም እራት ግብዣ በመቃወም በአሥርሺዎች የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በህብረት ድምጻቸውን ሲያሰሙ ውለዋል፡፡በመጨረሻም እነዚሁ የአፍሪካ መሪና ተወካዮች በከተማው እንደልባቸው ሲገበያዩ ፤ ሰንደቅ አላማቸው ባረፉበት ሆቴል ሲውለበለብ ፤ የወያኔ የነፍሰ ገዳይ ስብስቦች ግን አንዳቸውም ያልታዩ መሆኑን እና በአሜሪካ መንግስት ትዕዛዝ የሚገጥማቸውን አደጋ በመስጋት እንደ አይጥ አንድ ቦታ ተቀርቅረው እንዲሰነብቱ ተደርጓል፡፡

Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC. 20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላለን። ለቀለም ፣ለሹርባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ሰራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon




ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-4217 |
| ኢሜል፡ | espic@aol.com |
| ፖስታ፡ | EPRP<br>P.O. Box 73337<br>Washington, DC. 20056 |
| ድረ ገጽ፡ | eprp.com |

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-5832 |
| ኢሜል፡ | eprpylnew@gmail.com |
| ፖስታ፡ | EPRPYL<br>5309 Georgia ave.<br>Washington, DC. 20011 |
| ድረ ገጽ፡ | eprpyl.com |

**ባለፉት ተከታታይ ዕትሞች ፣ በዚህ ዐምድ ሥር ሲነበብ የከረመዉን ደማቁን የነጌሌ ቦረና የኢሕአፓ ወጣት ሊግ (ኢሕአወሊ) አባላት ገድል እነሆ ደመደምን ። እኛ በጽሑፍ እናስፍረዉ እንጂ ፤በዚያ ወርቃማ ትዉልድ የቆየልን አገርንና ወገንን የማፍቀር እጹብ ድንቅ የተጋድሎ ታሪክ በደምና በህይወት መሥዋዕት ደማቅ ቀለም ነዉ የታተመዉ ። ተወደደም ተጠላም ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተወራረሰ ፤ ከከሃዲዎች ሁሉ ጋር በኀሊና ሸንጎ ተሟግቶ እየረታ የሚበረታ ፤ የጠራ ኢትዮጵያዊ የእዉነት መስመር ስለመሆኑ ጥርጥር የለዉም ። በዚሁ ዓላማ ጠገግ ፤ በቀጣይ ባለተራነት ፤ አገራቸዉንና ወገናቸዉን ያሉ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሴት ልጆች በፍቅር፤ በዉበት፤ በጠነከረ እምነትና ወኔ አስጊጠዉ ካስቀሩልን አያሌ ሕዝባዊና አብዮታዊ የተጋድሎ ታሪኮች ዉስጥ አንዱን ይዘን ቀርበናል ። ከትረካው ወጣኒነት እስከ መግቢያዉ ድረስ የድንቅ ብዕሩን ትሩፋት ላቋደሰን ደራሲ ለባቢሌ ቶላ ፤ እንዲሁም በኀደለበት ሁሉ ለሞላችሁልን የጓድ ቆንጂት ቤተሰቦች ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ ።**

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

*የታመነችለት ታላቅ ዓላማ የርሷን መኖር ይሻዉ እንደነበረዉ ሁሉ ፤ ትርሲትም በሕይወት ኖራ የበለጠ ለመታገል ስትል ፤ ከቀዩ ሽብር ፋሺስታዊ ፍጅት ለመትረፍ ቆርጣ መነሳቷን ከጽሑፏ እንረዳለን ። በሥራ የተረጎመችዉም ይህንኑ ነበር ፦ በቃል ሳይሆን - በግብር ፤ ከሩቁ ሳይሆን - እዚያዉ ድረስ ሄዳ ከሕዝቡ ጎን በመቆም ፤ ለድለላ ሳይሆን - ችግር ጉስቁልናቸዉን አብራ እየኖረች በመካፈልና ሞታቸዉን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ፤ በጀግንነት ኖራ በጀግንነት አርፋለች ። በበኩሌ ፤ ትርሲትን ለማወቅ በመቻሌ ክብር ይሰማኛል ። (ባቢሌ ቶላ)*

### ፩

የትም ሆነ የት ፤ አንገቱን ዘወር አድርጎ ለተመለከተ ሁሉ ፤ ብረት ለበስ መኪናዎች - በየዐይነታቸዉ ከዐይን ይገባሉ ። ሬንጅ ሮቨሮች ፤.... ጂፖች ፤ .....ሽፍን ቮልስ ዋገኖች ፤ ... ወዘተ ......በዝግተኛ ፍጥነት ጎዳናዎችን ያካልላሉ ። እያንዳንዱ ተሽከርካሪ እስካፍንጫቸዉ የታጠቁ ወታደሮችንና የደህንነት አባላትን አጭቆ ጭኗል ። የስቪል ልብስ የለበሱቱ ፤ ከጨርቅ የተሰፉ ባርኔጣዎችን ከመድፋታቸዉም በላይ ዘናጭ ጥቋቁር መነጽሮች አድርገዉ የጃኬቶቻቸዉን ኮሌታዎች ወደ ላይ ቀስረዋቸዋል ። ይህም ፍጹም ተራ ዱርዬ ወይም በመናኛ ሲኒማ ዉስጥ የሚገኝ ገጸ-ባህሪ አስመስሏቸዋል ። የኮማንዶ ሬንጀር የደንብ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ዕይታ በራሱ በፍርሃት ያንዘፈዝፋል ። በጂፖቹ ላይ የተጠመዱባቸዉን ቢ አር መትረየሶች ፤ እንዲሁም በተሽከርካሪዎቹ ክፍት መስኮቶች ወደ ዉጭ የተወደሩትን፤ የደህንነት ታጣቂዎቹ የታጠቋቸዉን የኤኬ47 (ክላሺንኮቭ) እና የተለያየ ስሪት ያላቸዉን ጠብመንጃዎች አፈሙዞች በቅርብ ሆኖ መመልከት መላ አካላትን የሽብር ብርክ ያስይዛል ።
ታጣቂዎቹ ተሳፋሪዎች ፤ በየጎዳናዉና በየመሿለኪያዉ የሚተላለፈዉን እያንዳንዱን ሰዉ በአሻጋሪ ሆነዉ በጥንቃቄ ለመመልከት እንዲችሉ ተብሎ ፤ ተሽከርካሪዎቹ ከልጅ ሩጫ ባልተሻለ ፍጥነት ነበር የሚጓዙት። ደርግ ለሚቆጣጠረዉ የሠራተኞች ማህበር (መኢሠማ) ሊቀ መንበር የነበረዉን ተመስገን ማዴቦን ለመዘከር ፤ እነዚያን ጥልማሞት መኪኖች “ የማዴቦ ፈረሶች፤’’ እያልን ነበር የምንጠራቸዉ ። ማርቆስ ሀጎስን የመሳሰሉ ሀቀኛ መሪዎቹ በአገዛዙ ከተገደሉ በኋላ እንዲፈርስ በተደረገዉ አይበገሬ የኢትዮጵያ የሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ ) ምትክ ለተቋቋመዉ መኢሠማ በሊቀ መንበርነት የተሰየመዉ ተመስገን ማዴቦ ፤ በመዲናይቱ አዉራ ጎዳናዎች ላይ የሚካሄዱትን “አስሶ የመደምሰስ” ተልዕኮዎችም በግንባር ቀደምነት ከሚያስፈጽሙት ዐረመኔ ፋሺስቶች አንዱ ነበር ። ያለ አንዳች ተጠያቂነት እንዳሰኛቸዉ ለመግደል ወይም ለማሰር ልዩ ፈቃድ የተሰጣቸዉ በደም ጥም የናወዙ ነፍሰ ገዳዮች፤ በይፋ የተሰማሩባቸዉን ግድያን ፤ ስየልንና እስራትን የሚያካትቱትን የ “ነጻ ርምጃ” ተከታታይ ዘመቻዎች ካስጀመሩት ሰዎችም አንዱ ተመስገን ነዉ።

ተመስገን ማዴቦ ፤ ዘወትር አመሻሽ ላይ ብረት ለበሱን አጀቡን አስከትሎ በመኢሠማ ዋና ጽ/ቤት አቅራቢያ የሚገኙትን አዉራ መንገዶች የማካለል ልማድ ነበረዉ ።እዚያም ፤ ኤኬ-አርባ ሰባት (ካላሺን) ጠመንጃዉን አንግቶና ሁሌም ተፈጥሮአዊ ክፋቱን ከማይደብቅ የፊቱ ገጽ ላይ ዕብሪቱን አጉልቶ እያስነበበ ፤ ያጋጠመዉን ሁሉ እያስቆመ ይፈትሻል ፤ በምርመራ ጥያቄ ያዋክባል ፤ ይረሽናልም ። ድንገተኛ ሞት በተለመደበት በዚያ ዘመን ፤ በማዴቦ የግድያ ቡድን ከተደበደቡ በኋላ በነጻ ለመለቀቅ መቻል ከመታደል እኩል ነበር የሚቆጠረዉ ።

## ትናንትና

በ፩፱፻፷፱ ዓ.ም ኅዳር ዉስጥ ደንገዝገዝ ባለ አንድ ምሽት በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል አጠገብ ከሚገኘ ጎዳና ላይ ፤ ነፍሰ ገዳዮቹ ቡድኖች “ የአናርኪስቶች አለባበስ ” ብለዉ በሚጠሩት አኳኋን ተላብሰን በመዘጋጀት ወጥመዳችንን አጠመድን ። የሚያድነዉን ወገን ከሩቁ የተመለከተዉ የማዴቦ ገዳይ ቡድንም በፍጥነት መኪናዉን አቆመ ። ወዲያዉኑም ተመስገን ማዴቦና ሁለት አጃቢዎቹ ታዳኙ ወደሚገኝበት ሥፍራ ዘልለዉ ለመዉረድ የመኪናቸዉን በሮች ከፈቱ ። በዚህ ጊዜም አንድ ሁለት ዑዚ ጠመንጃዎችንና አንድ የእጅ ቦምብ ታጥቆ የወጣዉ የመከላከያ አህዳችን ፤ ተመስገን ማዴቦንና አጃቢዎቹን ከመደምሰሱም በላይ አንድ የተበላሸ ካላሺንኮቭ ጠመንጃ ማርኳል ። በምርኮ የተገኘዉ ያ ጠመንጃ ጥገና ተደርጎለት ቀጥለዉ በተከናወኑ ግዳጆች ላይ አገልግሎት ሰጥቷል ። የመከላከያ አህዳችን ግዳጁን ከፈጸመ በኋላ ፤ ጥቂት ፈንጠር ብሎ የመከላከያ ሚኒስቴርን ከብቦ ከሚጠብቀዉ የብረት ለበስ ዘብ አፍንጫ ሥር በአስደናቂ ፍጥነት አምልጦ በመዉጣት በተሳካ ሁኔታ ሊሰወር ችሏል ።
ታማኝ ሎሌዉን ያጣዉ የደርግ አገዛዝ ፤ በ “አብዮት አደባባይ” ፤ ቀጥሎም “ በተለይ ለአብዮታዉያን ” በመደበዉ የመቃብር ሥፍራ ፤ ከዚያ ቀደም የተከናወኑትን ሁሉ የሚያስንቅ ደማቅ የቀብር ስነ ሥርዓት አከናወነ ። በየስነ ሥርዓቱም ላይ እንደተለመደዉ ፤ በመከላከያ አሀዶቻችን በሚገደል በእያንዳንዱ “ አብዮታዊ ” ምትክ ሺህ “ ሥርዓት አልበኞችን ” ለመግደል የገቡትን ቃል ኪዳናቸዉን አድሰዉታል ። ልክ የጀርመን ናዚዎች የተነሳባቸዉን ሕዝባዊ ተቃዉሞ ለመጨፍለቅ ከወሰዷቸዉ የጅምላ ግድያዎችና የኃይል ርምጃዎች ጋር የሚመሳሰል ተግባር ነበር ። ሕዝባችን እንደሚያዉቀዉ ፤ በእኛ በኩል ራሳችንን ከጥቃት ለመከላከል ለወሰድናቸዉ ርምጃዎች በሙሉ መንስዔዉ የአገዛዙ የማያባራ እመቃና ገደብ የለሽ ግድያ ነበር ። የደርጉ አገዛዝ የመጀመሪያዉን ጥይት የተኮሰ ከመሆኑም በላይ በፖለቲካዉ መስክ በምናደርገዉ ትግል እያቸነፍነዉ መሆኑ ግልጽ እየሆነ እንደመጣ ፤ “ ሥርዓተ አልበኞችን ለመደምሰስ ” የጭፍጨፋ ዉሳኔዉን አሳልፏል ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የሚሄደዉ መንግሥታዊ እመቃና ሽብር ከጅምሩ ከወታደራዊዉ አገዛዝ ተፈጥሮ ጋር በጽኑዉ የተሰናሰለ ባህሪ ቢሆንም በስፋትና በተጧጧፈ መልክ መካሄድ የጀመረዉ አዲሱ የእመቃ ዘመቻ በከተማይቱ ዉስጥ በየትኛዉም ሥፍራ ጎልቶ የሚታይ ሊሆን በቅቷል ። “ የማዴቦ ፈረሶች” ፤ ቁጥር በማይገልጠዉ መጠን ፤ ሞትን ለሁሉም አዳረሱ ። የግብር ይዉጣ ፤ ሥፍራ ሳይመርጡ የተሰቀሉትና በፈኩና ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ቀለሞች የተጻፉት መፈክሮችም ይህንኑ የሚለፍፉ ነበሩ ። .... “ ቀዩን ሽብር እናፋፍማለን /”.... “ ዴሞን በዲሞትፎር ግደል /” .... ( ዴሞ ፤ የኢሕአፓ ልሳን ከሆነዉ “ ዴሞክራሲያ ” የተፈጠረ ምህጻረ ቃል ሲሆን አገዛዙ የኢሕአፓን አባላት በጥቅል የሚጠራበት ስያሜ ሊሆን በቅቷል ። )
ከየካቲት ፷፮ የካድሬዎች ማሰልጠኛ ት/ቤት ፤ከህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና ከአምስቱ “ ህቡዕ ” ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች የተመራረጡ የርዕዮተ ዓለም አቀንቃኞቻቸዉ ፤ እስከ አፍንጫቸዉ ድረስ ታጥቀዉ ፤ በየከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቱ ፤ በየፋብሪካዉ ፤ በየመሥሪያ ቤቱና “የኢሕአፓ ምሽጎች” በየሚባሉት ሥፍራዎች ሁሉ ተሰራጩ ። .... { አምስቱ “ ህቡዕ ” ድርጅቶች ፤... ፩/ የመንግሥቱ ኃ/ማርያሙ አብዮታዊ ሰደድ ፤... ፪/ የኃይሌ ፊዳዉ መኢሶን .....፫/ የባሮ ቱምሳዉ ኢጭአት....፬/ የተስፋዬ መኮንኑ ማሌሪድ .... ፭/ የሠናይ ልኬው ወዝ ሊግ ናቸዉ ። } “ ሥርዓተ አልበኞችን ” የመመንጠር ዘመቻቸዉንም ተማሪዎችን ፤ ሠራተኞችን ፤ ወዘተ....... በስብሰባ አዳራሾች ዉስጥ ከሰበሰቡ በኋላ ተሰብሳቢዉን ሕዝብ በማስፈራራትና ሽብር በመንዛት ጀመሩት ። ማስፈራሪያዎቹና ጣጠኛዉ የ“ አጋልጥ - ተጋለጥ ” ክንዉኖችና በየጣልቃዉ የኢሕአፓን አቋሞችና መርህ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ርባና ለማሳጣት ይቀርቡ የነበሩት ተራ መሟገቻዎች ከታቀደላቸዉ ዉጤት በተቃራኒዉ ፤ የአገዛዙን ካድሬዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ድኅነትና ግራ የተጋባ አቋም የሚያጋልጡ ነበሩ ። ዋና የማሳመኛ ዘዴአቸዉም ቢሆን ያዉ ሽብር እንጂ ሌላ አልነበረም ። እያንዳንዱን ተጠርጣሪ “ሥርዓተ አልበኛ” እያዳፉ ከስብሰባዉ አዳራሽ ካስወጡት በኋላ አካላዊ እንግልትና ድብደባ ይፈጸምበታል ፤ በርሽናም ያስፈራሩታል ። አዳራሹ ዉስጥ ለቀሩት ደግሞ ወደ አብዮቱ ሠፈር ካልተቀላቀሉ በቀር ተመሳሳይ ስቃይ እንደሚጠብቃቸዉና ቀይ ሽብር እንደሚፋፋምባቸዉ ይነግሯቸዋል ።

ጥቂት ቆይተዉ ፤ በከተማ ነዋሪዎች ማህበራት (ቀበሌዎችና ከፍተኛዎች ) ፤በፋብሪካዎች ፤በተጎራባች የገበሬ ማህበራትና በሌሎች ተቋማት ሥር የሚገኙ “አብዮት ጠባቂዎች” ሳይቀሩ ጡንቻቸዉን ማሳዬት ጀመሩ ። የፍሳሽ መዉረጃዎችንና ሸሸጉን የከተማይቱን ገጽ ተጠግተዉ የሚኖሩትን ወስላቶችና ቀንደኛ ቀንደኛ ወንጀለኞች መልምለዉ ፤ አሠልጥነዉና አስታጥቀዉ በስራቸዉ ካሰለፉ በኋላ በእኛ ላይ ያቀዷቸዉን የጥቃት ዘመቻዎች ከፈቱብን ። ዘወትር ማለዳ ላይ እነዚሁ ነፍሰ በላዎች ፤ ጸረ - ኢሕአፓ መፈክሮችን በጩኸት እያሰሙና ለ“ሥርዓተ አልበኞች” ሞት የገቡትን ቃል - ኪዳን እያኹጎደጎዱ የሠልፍ ልምምድ ያደርጋሉ ። እነዚህ ልምምዶች በሕዝቡ ልብ ዉስጥ ፍርሀትን ለማስረጽ ታቅደዉ የሚከናወኑ ናቸዉ ። ካድሬዎቹ ኤኬ አርባ ሰባት (ክላሺንኮቭ )ና ሌሎች ሙሉና ከፊል አዉቶማቲክ ጠመንጃዎችን የሚታጠቁ ሲሆን የአብዮት ጥበቃዉ ነብሰ- በላዎች ደግሞ እንደ ቺኮዝ ባሉ ባለቃታ መሣሪያዎች ይገለገላሉ ። ግድያን በሚመለከት ግን ሁሉም እኩል እንዲፈተታቸዉ ለመግደል የሚያስችል ፈቃድ ነበራቸዉ ።

**ይቀጥላል........**

# ነጻ ሀሳብ

## የሰርገኛ መጣ በርበሪ ቀንጥሱ ፖለቲካ

የፍኖተ ዴሞክራሲ ሀተታ ፧- ሐምሌ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. የተላለፈ

ያለው ተጨባጭ ሁኒታ እየከፋ ሲመጣ ወይም ድንገተኛ ሁኔታ ተፈጥሮ ንዴትና ቁጭት ሲያይል ቀቢጸ ተስፋ የሚያመጣው ሰርገኛ መጣ በርበሪ ቀንጥሱ ዓይነት ሁኔታ አለ ። የታየ ነው፤ ወደፊትም ሊጠበቅ የሚገባው ። ችኮላው ግን ለትግልም ለሰርግም የሚጠቅም አይሆንም ። ቀደም ነበር እንጂ ለክቶ መደቆስ የተባለውን መርሳት አይገባም ።

በአሁኑ ጊዜ ጎልቶ የሚታየው ድክመት ታሪክና ተጨባጭ ሁኔታን ጠንቅቆ አለማወቅ ወይም ጭራሹኑ በዳበሳ ጉዞ ላይ መተማመን ነው ። ሁኔታዎችን ባለማወቅ ታጅሎ ያለ አንጎል የሚተልመው መፍትሄ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ መሆኑ ደግሞ የማይቀር ነው ። ለምሳሌ ድርጅቶች በየጊዜው ሊተባባሩ ጥረው ውጤትን ቢያስገኙም የተፈለገውና ወያኔን ሊያወድም የሚችለው የጋራ ጥረት እውን ሊሆን አልቻለም ። ለዚህም በቂ ምክንያቶች አሉ --መኖራቸውን ግን የማያውቁ ናቸው ዛሬ ስለ ህብረት መፍትሔ ሊሰጡ መድረክ ይዘው የሚገኙት ። ህብረትን እውን ለማድረግና ያለፈውን ስህተት ላለመድገም ታሪክና ሂደትን፤ የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ድክመቶችን ማወቅ የግድ ይሆናል ። ይህ ባልተደረገበት መፍትሔ መሻት ወይም ማቅረብ ጠቀሚታ የለውም ። በቅርቡ ለምሳሌ በአንድ የድርጅት መሪ መታፈን የተነሳ በዚህ ዙሪያ በአስቸኳይ ግንባር ይመስረት የሚሉ ክፍሎች አሉ ። ህብረት በዚህ ውሱን ጉዳይ ዙሪያ ሊመሰረት የሚችል ካልመሆኑ ሌላ የህብረት ችግሮች በዚህ መንገድም የሚፈቱ አይደሉም ። ይፈታሉ ብሎ ማመን ራስን ማሞኘት ነው ። በበኩላችን ደግሞ ይህን መቀበል የምንችል ባለመሆናችን ሀቁ ቢመርም ፊት ለፊት ማየቱን እንመርጣለን ። ህብረት ያልተቻለበት ምክንያቱ ብዙ ነው ። ተሞክሮ ያቃተበትም፤ ያልሰራበትም ምክንያት ውስብስብ ነው ። አንዳንዶች በአሁኑ ጊዜ ህብረት ያስፈልጋል የሚሉት ቀደም ብለው ህብረትን ያፈረሱ መሰሪዎች ናቸው። ሕዝብ ተባበሩ ወይም ተሰባባሩ ብሏል ብለው ሲቀልዱብን የቆዩ ናቸው ።

በኢሕአፓ ላይ ሁሉን ማላከክ ልማድ ሆኗልና የህብረት ጥረቶች ሁሌም የሚጓደሉት ድርጅቱ እኔ ልቆጣጠር፣ ልዘዝ ስለሚል ነው ያሉ ጥቂቶች አልነበሩም። ድርጅቱ ግን በእኩል ደረጃ በአንድ ድምጽ ደረጃ ተወስኖ ህልውናቸው አጠያያቂ ከነበሩ ቡድኖችም ጋር የሰራ መሆኑን ማስታወስ አይፈልጉም ። ሕብረትን ለመመስረት በተካሂደው የሁለት ዓመት ጥረት ድርጅቱ ያደረገው አቢይ አስተዋጾ ያታወቃል ። ሕብረት በ 15 ድርጅቶች ሲመሰረትም የነበረው ድምጽ አንድ ነበር ። ይህን ሕብረት ከመመስረቱ ለማፍረስ የተንቀሳቀሱት ሁለት ሊሎች ድርጅቶች መሆናቸውን ታሪክ ይመዘግባል ። ቅንጅት ብለውም ሲቋቋሙ እንዲሁ ፉክክር አንጂ ህብረትን አላስቀደሙም ። ቅንጅት ራሱ እንዴት እንደፈረሰ ምስጢር አይደለም ። ሕብረትና ቅንጅት በጋራ አቅዋም ይዘው የ1997ን ምርጫ ውጤት እንዲያስከብሩ ጥረት ሲደረግ የለም አሻፈረን ወደ ወያኔ ጉያ እንገባለን ብለው ሕብረትንም ያፈረሱት ሆነ ትግልና ያዳከሙትን ሁሉ ያውቃቸዋል። ዛሬ እነዚሁ ሀፍረተ ቢሶች ተመልሰው ህብረት ቢሉ ማን ሊሰማቸው ነው ? ታይተው ተፈትነው ውዳቂና ከሀዲ ከተባሉ ጋር ተመልሶ መተባባር ሊሞከር ቀርቶ ሊታሰብም የሚገባ አይደለም ። ከታሰበና ከተሞከረ ግን ከስህተትና ከተመክሮ ጭራሽ አለመማር ይሆናል ። በህብረት ደረጃ ለምሳሌ ከለየላቸው ደርጎች ጋር፤ ከፊውዳሎች ጋር፤ ከወያኔ መስራቾችና ከነጻ እርምጃ አቅንታኙና ደም አፍሳሾች ጋር ሳይቀር ሀገር ትቅደም ተብሎ ለመተባበር ሙከራዎች ተደርገው ነበር። ግን ድመት አመሏን አትረሳም ሆኖ መቅረቱን ታሪክ መዝግቧል። ለማንኛውም ግን ኢሕአፓ ችግር ፈጣሪ እኔ ከሆንኩ እነሆ ሚዳውም ፈረሱም ያው ተባበሩ እስቲ ብሎ ራሱን ሲያገል የታየ ተዓምር የለም ። በዚህ በዚያ ሁሉም ራሱን የትብብር ማዕከል አድርጎ ቢሰየምም የተገኘ ውጤት አልነበረም፤የለም ። የችግሩ ምክንያት ድርጅቱ ሳይሆን ሌላ ነው ።

ሕብረት ይመሰረት ዘንድ መጀመሪያ ድርጅቶች ህልው መሆን አለባቸው ። የከዚህ በፊት ጥረቶች አንዱ ችግር ራሳቸውን ድርጅት ብለው የሚጠሩት ሲመረመሩ የሶስት አራት ሰው ስብስብና አቅመ ቢስ መሆናቸውም ነው ። በእኩልነት ወይም በአንድ አንድ ድምጽ ይሰራ ስለተባለም ተደምረው 20 አባል የሌላቸው ገዘፍ ያሉትን ድርጅቶች አቅጣጫን አካሂድም ወሳኝ ሆነዋል ። ቡድኖቹ አባል አልባ በመሆናቸውም በየቦታው ስራው የግድ በአንድ ድርጅት ላይ ሲወድቅ ድርጅቱ ህብረቱን ተቆጣጠረው ለማለት እሽቅድምድም ሲካሂድም ታይቷል ። ህልውናቸው የደበዘዘና በትግእስትም ቢፈተሽና በማጉያ መነጽርም ቢታይ የለሁም እያለ ከነዚህ ዓይነቶቹ የይስሙላ ድርጅቶች ጋር ማበር ትግልን መጥቀም ሳይሆን ውሎ አድሮ ማደናቀፍ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ። ታይቷልም ። ሕብረት ምስረታ በሁሉም አቅዋም ላይ አንድ መሆንን ባይጠይቅም በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ግን ስምምነት መኖሩ ወሳኝ ነው። መሰረታዊ ጉዳዮች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

- ትግላችን በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያው ስርዓት ለማስፈን ነው፤
- በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ግልጽ አቅዋም፤
- ወያኔን በማስወገድ ላይ ግልጽ አቅዋም
- በሕዝብና በሀገር ሉዓላዊነት ላይ ግልጽ አቅዋም

ወይም የተስማማ አቅዋም ያስፈልጋል ። ይህ ባልሆነበት ህብረቱ ሳይከካ ተቦካ ሆኖ ወዲያውኑ በአፍጢሙ ይደፋል ። ኢዲሃህ ወይም ሕብረት ሲመሰረት የግል ስልጣን ፈላጊዎችና አሊያም ለወያኔ ያደሩ በውስጡ ነበሩና ሳይውል ሳያድር ፍርሻ ተጠናውቶታል ። ለምሳሌ ኦነግን ለማቀፍ የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ የከሸፉት ኦነግ በኢትዮጵያ አንድነት የማያምን በመሆኑና ለቀና ህብረት ዝግጁ ባለመሆኑ ነው ። ከቅንጅት ጋር መሰረትኩት ያለው ህብረት ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ወይም ከዚያ ወዲህ የዚሁ ቡድን አንጃዎች ከሊሎች ጋር መሰረትን ያሉት ትብብር መና ሆኖ የቀረው ለዚሁ ነው ። ግልጽና ቁርጥ ባለ መልኩ--የቃላት ጨዋታ ሳይሆን-- ኦነግ በኢትዮጵያዊነትና በሀገር አንድነት አምኖ ሊታገል ካልተነሳ የኢትዮጵያዊ ህብረት አካል ይሆናል ብሎ ማሰብ ማመንም የሚቻል አይደለም ። ከወያኔ ጋር ዕድል ፈልጎ ሊተቃቀፍ የሚፈልግ ድርጅት (ልጅ የተሰጠውን ተቀብሎ ለተጨማሪ ያለቅሳል ያለውን አድርባይ የሆነ ድርጅት መሪ ማስታወስ ይበቃል ) ወይኔ ከነስርዓቱ መወገድ አለበት ብሎ ከሚያምን ጋር በህብረት ሊዋቀር ሊተባበር አይችልም ። ከወያኔ ጋር በምርጫ በመወዳደር ብቻ ነው የትግላችን አልፋ ኦሚጋ የሚልና ወያኔን በሁለገብ ትግል እንፋለመው የሚሉ በህብረት ሊጣመሩ አይችሉም። በአንድ አቅጣጫ በአንድ ትኩረት ሊጓዙ ይከብዳልና ። ለምሳሌ የወያኔን የበላይነትና ሕገ መግንስት የሚለውን ተቀብለን፤ ፈርሙ ያለንን ፈርመን በስሩ እንንቀሳቀስ ያሉትን አባሎች በኢሕአፓ ውስጥ ሽንፈታቸውን ተቀብለው መቀጠል አቅቷቸው ወደ አንጃነት ዝገው ድርጅቱን ጥለው በመሸሽ ሊጎዱት ቢጥሩም እነሆ ከስመው ቀርተዋል ። በአንድ ድርጅት ቀርቶ በአንድ ህብረት መሰረታዊ የአቅዋም ልዩነት ካለ አብሮ ለመታገል የሚቻል አይደለም ።

በድርጅቶች መሃል ህብረት መመስረት ያልተቻለበት አንዱ ሌላ ችግር የባዕዳን ጣልቃ ገብነትን የሚመለከት ነው ። ከሆነ ድርጅት ጋር ካበርን ባእዳን ደስ አይላቸውም፤ይቆጣሉ፤ እርዳታ ያቆማሉ ብለው ስለሚፈሩ--ፍርሃታቸውም መሰረት የለውም ማለት አይቻልም - በአፋቸው ሕብረት ቢሉም በተግባር ግን ከመተባባር ጥረት ይሸሻሉ ። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ቀድሞ ተቃዋሚ የነበሩትን አሚሪካ እዝ ሰጥቶ ከወያኔ ጎን ማሰለፉን የምናውቀው ጉዳይ ነው ። ይህ አሚሪካ የተባለ ሀይልም ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ስለማይወድ፤ የወያኔን የክፍፍል ፖለቲካም የሚደግፍና በተለይም ኢትዮጵያንና አፍሪካን በጎሳ ለመከፋፈል የሚጥር በመሆኑ ሀገር ወዳድና ኢትዮጵያዊ የሆነ ድርጅቶችን ይታገላቸዋል፤ ሊያጣፋቸው ይጥራል እንጂ አይደግፋቸውም ። በአሁኑ ጊዜ አሚሪካ በተቃዋሚ ጭምብል በህዝብ ጎራ የተከላቸውን ማየቱ ብቻ ይበቃል። የአሚሪካው ሳያንስ እንደ አቅሚቲም ሻዕቢያም ድርጅቶች ላይ የአዛዥ ናዛዥን ቦታ ይዞ በድርጅቶች ላይ ጎጂ ጣልቃ ገብነትን ሲያካሂድ መከረሙንም መጥቀስ የሚቻል ነው ። ሌሎች ሌሎች ችግሮችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ቁም ነገሩ ግን የህብረት ምስረታ ችግሮች በይዘታቸው ተመርምረው መፍትሄን ይፈለጋሉ እንጂ በድንገተኛ ስሜት ወይም ንዴት ህብረትን መስርቱ ብሎ እዝ መስጠቱ ወይም ይሆናል ብሎ ማመኑ አላዋቂነትን ጠቋሚ ነው ። ለጋራ ተቃውሞ በጋራ ተሰልፈው ልዩነታቸውን ያውም በባእዳን ፊት በዚያው የሚያሳዩ አሉ ። እናብር ባለው አፋቸው ሊሎች ድርጅቶችን ሲዘልፉና ሊከፋፍሉ ሲጥሩም --በዚህም ወያኔን ሲጠቅሙ --ያየነው ሕጸጽ ነው ።

ይህን ሁሉ ያልነው እንዳለ ሆኖ አሁንም ወያኔን ለመገርሰስ የታጋይ ሀይሎች ህብረት ማስፈለጉ ጥርጥር የለውም። ክዚህ በተያያዘም ሆነ በፊትም ግን ሕዝብን በጋራ አቅዋም ላይ ማስተባባሩ ክብደት የሚሰጠው ነው ። ሕዝብን መከፋፋልና ኢትዮጵያን ማፍረስ ዋና ዓላማቸው የሆኑ ሀይሎች ሕዝብን ሊያስተባብሩ አይጠበቅም። ሕዝብ በህብረትና በጋራ እንዲነሳ በብሄረሰብ ሆነ በሃይማኖት እንዳይከፋፈል መቀስቀስ፤መታገልና በኢትዮጵያዊነት ዙሪያም ማደራጀት ያስፈልጋል ። ማለትም ሁሉም አገር ወዳድ ድርጅቶች ከህዝብ አንጻር አስተባባሪና ህብረት መስራች አቋም ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው ። ይህ ሁሉ የሚጠነጠነው ወያኔን ማረቅ ማረም የማይቻል በመሆኑና ያለውም ብቸኛ አማራጭ ይህን ከይሲ ቡድን ማስወገድ ብቻ በመሆኑ ነው ። ከወያኔ ጋር ሰላምና ዕርቅ የሚሰብኩ ሕዝብን የሚያደናግሩና ትግልንም የሚጎዱ ናቸው። የ23 ዓመት ተመክሮ ይህን ሀቅ ተቀብሉ ይለናል ። ወያኒ ለተጨማሪ ዓመታት ሀገርን ሊያጠፋ ዕድል ልንሰጠው አይገባም ። ሀገር አድን ትግሉ የሚጠይቀውን ህብረት እውን ለማድረግ መመኘቱና መጣሩ ተገቢ ሲሆን ችግሩን አቅልሎ በመያዝ ወይም ለመያዝ በመነሳት ቀቢጸ ተስፋን ለመንገስ ዕድል ባንሰጥው የሚመረጥ ይሆናል ። ህብረት ለምን? ህብረት እንዴት? በዚህ ላይ መግባባቱ ይቅደም። የጅብ ችኩል ቅንድ ይነክሳል እንደተባለው ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱም ብልህ ፖለቲካ ወይ አቋም አይደለም

## ድልን ያራቁ ዋና ዋና ችግሮች

**የፍኖተ ዴሞክራሲ ሀተታ ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም. ተላለፈ)**

ዕብሪተኛ ቻይናውያን ላቡን ለሰአታት የሚያፈሰውን የሚያንጠባጠበውን ኢትዮጵያዊ ሰነፍ ብለው የመደብደብ መብት ሳይቀር በወያኔ ተሰጥቷቸዋል። ያሳዝናል፤ ያሳፍራል ። መቆጨቱና መጤሱ ግን ፋይዳ የለውም== በዳዮች ልብና ርሕራሔ የላቸውምና ። በደልን ነጋ ጠባ መደርደሩና ማላዘኑ ዋጋ የለውምና፤ ገዢዎች የተባሉት ህ.ሊናም ይሉኝታም

ከገጽ 3 የዞረ

**ዜና ከተባለ**

- በረከት ስምኦን ታሟል ከሚለው ዜና ጋር ተያይዞ በወያኔ ውስጥ ያለው ክፍፍል መባባሱ እያነጋገረ ነው ። የአዜብ ወደ ጎን መጣል ለስብሓት መጠናከር በሩን አልከፈተም። አዜብ በአሚሪካና እንግሊዝ ሆቴሎችና የንግድ ተቋሞችን እየመሰረተች ነው ሲባል በዴንቨር፤ በሂውስተን (ሉሲ ሪስቶራንት)፤ላስ ቪጋስ፤ ለንደን፤ዋሺንግተን ወዘተ ተጠቅሰዋል ። በተጨማሪ የትግራይ አውራጃዊነት ችግር አሁንም ወያኔን ተጠናውቶታል። የውጭ ሀይሎች ጣልቃ ገብተው የደብረ ጽዮን አንጃ ለምዕራቡ ይጠቅማል በሚል እየሰጡት ያለው ድጋፍም የራሱን ውስብስብ ችግር ፈጥሯል ። በተያያዘ ዜና ተፈራ ዋልዋም ቀኑን እየቆጠረ ነው ተብሏል።

- ወያኔ በጸረ ሻዕቢያ ትግል እንዳንሰማራ አደረገን የሚሉት የእርትራ ተቃዋሚ ሀይሎች ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሀይሎች ጋር ለመወያየት ፍላጎት እንዳላቸው አገለጹ ቢሆንም በሌሎች አፍቅሮ ኢትዮጵያ አላቸው ተብለው እንዳይከሰሱ በሚል ግን ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ አቅቷቸዋል ።

- የህብረት ጥረቶችን አሁንም ጸረ አማራ የሆነው ገብሩ አስራት፤ በመድረክና መኢአድ ውስጥ ያሉ ሰርጎ ገቦች ማክሸፋቸው ሲነገር በውጭ ሀገር ደግሞ የህብረት ደጋፊ መስለው ክፍፍልን የሚያናፍሱ መበርከታቸው ምስጢር አይደለም ተብሏል ። አሁንም ቃታ ያልሳቡና ባሩድ በጤሰበት ያልተገኙ ሳይቀሩ በብቻችን ታግለን እናሸንፋለን በሚል ግምት ውስጥ ራሳቸውን ከተው አሉ ።

- የአውሮጳ ህብረት በሚጠበቀውም ደረጃ ባይሆንም የወያኔን የመብት ረገጣ በቅርቡ አውግዟል። የአውሮጳ ማህበር ሀቁ ይነገር ከተባለ የወያኔ ዋና ደጋፊ ነው።

____________////____________

- ***ለወያኔ ውድቀት ያብቃን ።***

ከገጽ 6 የዞረ....

የላቸውምና። የሕዝብ ደም ጠያቂ ትግል፤መስዋዕትነት የተከፈለበት ትግል ለምንስ ድልን አልተቀዳጀም ብሎ መጠየቅ በጣም ተገቢ ነው ። ለዚህ አያሌ ምክንያቶች አሉ-- የወያኔ ሁለገብ ሻጥር አለ--ተለጣፊዎችን፤ አስመሳይ ተቃዋሚዎችን ያቀፈ፤ አወናባጅና አደናጋሪ እንቅስቃሴ ። ይህ ግን ሁሌም ሕዝብን ሊያደናግር አልቻለም፤ አልሆነምም ። ጸረ ወያኔ ሆነው ወያኔን በምሬት ሊታገሉ የተነሱትም ለወያኔ ድለላ ጆሮ የሰጡበት ጊዜም ጥቂት አይደለም ። ለሕዝብ ጎራ ድክመትና ትርምስ፤ ባለፈው ትውልድ የታየው ወኔና ቆራጥነት ዛሬ አጥቶና ደብዝዞ ለመገኘቱ ብዙ ምክንያቶች አሉ ። በደርግም በወያኔም ላይ ሀላፊነቱን መጫን ስህተት አይደለም ። ወታደራዊው አገዛዝ በቀይ ሽብር አንድ ትውልድ ከመምተሩ ባሻገር ዜጎች--በተለይም ወጣቱ -ከፖለቲካ በፍርሃት እንዲርቅ ድልዳሉን አዘጋጅቷል። ብሔረሰቦችን አቀፍና ኢትዮጵያ ያሉ ድርጅቶችን አሳዶና አጥቅቶ ሜዳውንና መድረኩን ለጠባቦችና ገንጣዮች ትቶላቸዋል ። ግለኝነትንም አስፋፍቷል ። ወያኔ የፈጸመብን ግፍና ሕዝብን በየፈርጁ መከፋፍሉ ያደረሰው ጉዳት ደግሞ ተርኩኝ የሚለን አይደለም--እየኖርነው ነንና ። ስለዚህም ደርግም ወያኔም ጎዱን ብንል ሀቁን መድገም ነው ። ደርግ ለወያኔ መንገዱን ጠርጎ ህዝብን አዳክሞ ኢትዮጵያን አስረከበው ብንል ሀቁን መናገር ነው። ደጋግመን ለማቅረብ እንደሞከርነው ግን ዋናው ትኩረታችን በራሳችን ውሳጣዊ ችግር ላይ መሆን አለበት። ይህን አቢይ እውነታ ስናቀርብና ጫና ሰጥተንም በስራ ልናውል ስንነሳ የሹም ዶሮዎችና አጫፋሪዎቻቸው፤ ከንቱ አንጀኞችም ተደምረው ድርጅቶች ተሰደቡ ወዘተ ብለው ኡኡታ ሲያሰሙ ታዝበናል ። የተሳሳቱና ብቃት የጎደላቸውን ወይም ተቃዋሚ ነን እያሉ ለወያኔ የሰገዱትን ክፍሎችንም አትንኳቸው ብለው ይከላከላሉ ። ለባዕዳን አድረው የተቀዋሚ ጎራውን ለጠላቶች የሚያጋልጡትንም እናጋልጥ ሲባል ተርሲኒ--ተከላካይ ሆነው ይጋተራሉ ። ይህ ደግሞ መደረግ ያለበትን የራስን ድክመት ምርምርም በአጭሩ ያስቀርና ተቃዋሚውን እንደተሸመደመደና ከድል እንደራቀ ያቆየዋል ። ድል ምነዋ ራቀን ስንል ግን የጠላትን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በተለይም የራሳችንን ይዘት መመርመር መገምገም ይኖርብናል ። ጠላትን እወቅ፤ በተለይም ራስክን እወቅ--መቶ ጦርነት ብትዋጋ መቶ ጊዜም አሸናፊ ትሆናለህና ተብሏል ። ስለዚህም ድል ለምን ራቀን ስንል የራሳችንን ድክመት በቅድሚያ ማየቱ የግድ ይሆናል ። ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል ። ራስን በማታለል ጠንካራ ድርጅት ነን፤ ወያኔ ደክሟል፤፡ ጦር ልናሰልፍ ነው፤ ወደ 45 ሺ ተዋጊ አሰልፈናል፤ ወዘተ እያሉ ደጋግመው ውሸትን እየጠረቁ (ዓይነታ ዋሾዎች ከፖለቲካ መቃብራቸው በቅርቡም ተነስተዋል ) ራስንም ሕዝብንም ማታለል በጣም ጎጂ ነው-- ከሃቅ ጋር አይገናኝምና-- ተራ ውሸት፤ድለላና ገንዘብ ለመመመንተፍ የታቀደ ነውና ።

ስለዚህም ሀቁ ይነገር፤ ድክመታችን ይታወቅና ወደ እርምቱ በፍጥነት እንገስግስ ። በሽታውን የደበቀ መድሐኒት አይገኝለትም ተብሏል ። አያሌ ዜጎች የተቃዋሚ ሀይሎችና የትግሉ ዋና ድክመት ትብብርና ህብረት መጥፋቱ ነው ይላሉ ። ትክክል ነው ። ለምን ግን ህብረት መመስረት አልተቻለም ለሚለው ዋና ጥያቄ መልስ መስጠት ያስፈልጋል ። አንዳንዶች ያለፉትን ተምክሮዎች ሳያውቁና ሳይገመግሙ ወደ ትችትና ውግዘት ይሮጣሉ ። ዘንድሮ ደግሞ በማያውቁት ታሪክ ላይ ትችት ማዥጎድጎድ፡ መጽሃፍ መጻፍ ስልጡን ፖለቲካ ተብሏል ። ያለፉት የህብረት ጥረቶችን በጥሞና መመርመሩና በጎና ድክመቱንም ማብጠርጠሩ ተገቢ ነው ። ዛሬ ህብረት ነን ሸንጎ ነን ወዘተ ከሚሉን አልፎ ያውም በ አሜሪካ (ነጻ በወጣ ምድር ሳይሆን እንደ አልጀሪያ ቪየትናም ወዘተ) የሽግግር መንግሥት ሊያቋቁሙልን የተነሡ ቀልደኞችም አሉ ። ህብረት ለምን አቃተ? ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን ። በተቀዳሚ መተማመን ስለሌለ። ለምን መተማመን ጠፋሳ ስንል ደግሞ የሕዝብ ጎራ ሊጸዳ ባለማቻሉ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ የፖለቲካ መድረኩ በነጋዴዎችና ግብዝ ምሁሮች ና የተራ መድረክ ሰዎች መጨናነቁ ነው ። ለምን እምነት ጠፋ ስንል ደግሞ የተቃዋሚው ጎራ ውስጥ ዋና ተዋንያን ነን ያሉት ታሪክ መጥፎ በመሆኑ ስምሪታቸውንና የሚሉትንም ማመን በጣም አስችጋሪ በመሆኑ ነው ። ትላንት ስንት ነፍስ ያጠፉ ወንጀለኞች የድርጅት፤ የቡድን ወይም የድረገጾች አባወራዎች ሆነው ሲሰየሙና ላንዳፍታ ይቅር በሉን ሳይሉ ሲቀጥሉ ማመንና መቀበል ያዳግታል ። ትላንት በወያኔ ውስጥ ዋና መሪ ሆነው ህዝብን ሲበድሉ፤ መሬት ሰርቀው ወደ ትግራይ ሲያጠቃልሉ፤ ጦርነትን ለእኛ ለወርቅና ጀግና ዜጎች ተዉልን ሲሉን የነበሩት፤ እነ ፕሮፌሰር አስራትን ያሰሩና ያሰቃዩ ዛሬ ለመጠነ ብዙ ውንጀላቸው ይቅርታ ሳይሉ ሳይጠይቁ እንምራችሁ ሲሉ መቀበሉና ማመኑ አዳጋች ይሆናል ። በተለምዶ አነጋገር ሂሳብ ማወራረድ መቅደም አለበት። ትግል ህብረትን ጠያቂ ነውና ለመተባበር ደግሞ መተማማን ያስፈልጋል ። ህብረት ህብረት ባዮቹ ም ለወያኔ ለባዕድም ያደሩ ናቸው ብሎ ጥርጣሬ ካለ አይኑን ሽፍኖና ተጫወቱብኝ ብሎ የሚሞኝ የለም ። ትላንት ጎዶቹ፤ ወላጆቹን ፤ ወዳጆቹን የገደለን አረመኔ ታጋይ አገር ወዳድ ብሎ መቀበል ቢሳነው ሊወቀስ አይገባም። ቂመኛ ሊባልም አይቻልም ። የተበደለ ቢያንስ ይቅርታ ልጠየቅ ማለቱ ተገቢ ነውና ። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ የወያኔ መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ ህዝብን በአጠቃላይና አማራውን በተለይ ሲሰድብ የነበረ ምሁር ዛሬ ታጋይ ሆኛለሁና ልስበካችሁ ሲል ማንስ ሊያዳምጠው ይችላል? መጋለጥ የለበትም ? ሰማያዊ የካድሬ ልብስ ለባሽና ታጣቂ ምሁር--ደርግ ኢሰፓ== ዛሬ ተገልብጦ ያንን ትውልድ እያወገዘ መሪ በሉኝ ሲል ወግድ ማለቱ ሲያንስ ነው ? መድረኩ የተያዘው በነዚህ አይነቶቹ ነውና ብልጥ ፈንጠር በል፤ ራቅ በል፤ ቢባል ምን ያጠያይቃል ። ትላንት ከወያኔ ጋር ሆኖ ዘረኛነትን ሲያራግብ የቆየው ዛሬ በተአምር ወያኔ ሆንኩ ማለት ብቻ ሳይሆን ሀቀኛ ሀገር ወዳዶችንም አሁንም እያወገዘ ግን ተቃዋሚ በሉኝ ሲል አለማመኑ ሲያንስ ነው ። ለዚህም ነው ለህብረት ጽዳት መቅድሙ የግድ የሚሆነው ።

ሁኔታም ሰውም ይለውጣል ይላሉ አንዳንዶች ። ብሩህ ተስፋ ደግ ነው-- ጨለምተኛ ከመሆን ። ቆሞ ማንቀላፋት ግን ጅልነት ነው --ጉዳዩ ሀገርን የሚመለከት ከሆን ደግሞ ጉዳቱ ከፍተኛ ይሆናል ። ሁኔታ ተለወጠ በሚል ክህደትን መስበክ ድግሞ አጉል ጮሌነት እንጂ ብልህነት አይደለም። ትላንት ዛሬ ኣይደለም ምን ያስገርመናል ያለው ጌታመሳይ ዶክተር ፕሮፌሰር በሉኝ ሲል አልተደመጠም ። ትላንት እርግጥም ዛሬ አይደለም-- ነገር ግን ትላንትም ዛሬም የማይቀየሩ እምነቶች አሉ ። ጊዜ ተለውጧል በሚል ሀገርን መካድ፤ ዘረኛ መሆን፤ በሕዝብ ላይ መፏለል አይቻልም። ዛሬ ዛሬ ነው ግን ለሕዝብ ጥቅም መታገል፤ ለደሞክራሲና እኩልነት መዋደቅ የሚቀየር አይደለም ። የሰለጠነ ፖለቲካ በሚል መደረግ ያለበትን ትግል፤ መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት መሸሽ አይቻልም ። ሰላማዊ ትግል በሚል --ያውም በሚገባ ሳይካሄድ-- ዘመናዊ ተዓምራዊ መንገድ የሚደረገውም ጫጫታ ከዚሁ ጋር የሚነሳ ነው ። ሕዝባዊ አመጽ ሌላ በወያነ ፍቃድ የለሆሳስ ሰልፍ ማድረግ ሌላ ። አመጽ ስንል ወደ የካቲት 66፤ ወደ ግብጽና ቱኒዝያ ትግል ይወስደናል ። ሰማይ ከምድር ቢጠጋ ወያኔ በሰላም ስልጣኑን አይለቅም። ከስራአቱ ተጠቃሚ የሆን ክፍል አለ ። ከብሯል፤ ደርጅቷል--ይህንንም ጥቅሙን ለመጠበቅ መዋደቁ አይቅሬ ነው። በመሆኑም ለስርዓቱ መቆየት ይታገለላል ብሎ መጠበቅ ያስፈልጋል ። በሰላማዊ ትግል መፍትሔነት እናምናለን ብለው ህዝብን ከወሳኙ ትግል ሊያርቁና ሊያዘናጉ የሚሞክሩት ክፍሎች ሀቁ ይነገር ከተባለ ሚዛን ያለውና ወያኔን አስጨናቂ ትግል--አመጽ ሲያካሂዱ ሳናይ ሀያ አመት አልፏል ። ሰላማዊ ትግል ሰላማዊ ትግል የሚባለው ይህንን በሕዝባዊ አመጽ ደረጃ ለማካሄድና ለማፋፋም ሳይሆን ቀደም ሲል ዱላ ይቅር መላ ይስፈን በሚል መደረግ ያለበትን ሁለገብ ትግል ለማደናቀፍ መሆኑ ዛሬም የሚታይ ነው ። እባብ ያየ በልጥ በረየ እንዲሉ ከዚህ በፊት ወያኔ በረቅቀ ተንኮሉ ተቃዋሚ ነኝ ባይ ቡድን መስርቶና መሪውንም ለወር ዝዋይ ወስዶ ስንቱን አውናብዶ የህዝብን ትግል በ1997 እንደጎዳ የምንረሳው አይደለም ።

ስለዚህም አጠፉን ማሩን አልሰማ ብሏልና፡ ይባስ ብለው የቀድሞ ጸረ ሕዝብ ወይም አድርባይ ጠባያቸውን ከቶም አልተዉምና፤ ዛሬም በአዲስ መልክ አስከፊውን አገዛዝ ከነዘረኝነቱ ሊቀጥሉ አቆብቁበዋልና ህብረት ህብረት የሚሉትን፤ በስራችን በዙሪያችን ተሰለፉ የሚሉትን ማመኑ አስቸጋሪ ሆኗል ። እምነት ከሌለ ደግሞ የጋራ ትግል የሚታሰብ አይደለም ። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ድርጅት በሉን፤ አስተባብሪ በሉን፤ አስተባብሪ በሉን፤ የየስድስት ወር በቃ አለቀ ደቀቀ፤ ነጻነት ሰበካችንን በጭፍኑ ተቀበሉን የሚሉት ድርጅት ሳይሆኑ የይስሙላና ምትሓት ናቸው ። ቢሰበሰቡ ጥላ አይጥሉም ። ግና ድርጅቶችን በማደናቀፍና አድርባይነትን ቦታ በመስተት ረገድ ሚና አላቸው ።ዋና ተልኮአቸውም የሚታገሉትን ድርጅቶች ማሳጣት፤ መከፋፈል፤ በረቀቀ መንገድም ወያኔን መደገፍ ነው--ወደዱም ጠሉም ።ድል የራቀን መተባባር አቅቶን ከሆነ መተባባር ያቃተን ደግሞ ተቃዋሚው ጎራ ከአተራማሾች መጽዳት ባለመቻሉ ነው ። በፖለቲካው መድረክ አለና ያሉት ብዙዎቹ ለደርግም፤ለወያኔም፤ ለባዕድም ያደሩ ናቸው ብንል ማጋነን አይሆንም። በዚህ መድረክ እገሌ ከማለቱ ብንቆጠብም መመሪያችን የጥላሁን ገሠሠ ሆድ ይፍጀው አልመሆኑ ግልጽ መሆን አለበት።

ስለዚህም ጎራችንን እናጽዳ። ሀቅኛ ሀግር ወዳዶች ከወንጀልኞችም ከቅጥረኞችም ርቀን ለመመካከርና ለመተባበር እንጣር። በአፋዊ ጦርነት ሳይሆን በተግባራዊ ትግል እንሰለፍ። ያኔ ድል የእኛ ትሆናለች። የሰማዕትንም ደም እናከብራለን ።

*በሳምንት ሁለት ጊዜ -ረቡዕና እሁድ- የሚተላለፉትን የፍኖተ ዴሞክራሲን ፕሮግራሞች www. Finote.org ያዳምጡ;። በየሳምንቱ ቅዳሜ በ2፡00 PM የሚተላለፈውን የፍኖተ ኅብረት የኢሕአፓ ድምፅ ፕሮግራም እንዲሁም በ www. Finote.org ድረ ገጽ ማግኘት የሚቻል ሲሆን በተጨማሪ በቀጥታም ሆነ በማንኛቸውም ጊዜ 401-347-0175 በመደወል ማዳመጥ ይቻላል።*

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

ሐምሌ 15 ቀን 2006

## ወያኔ በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰደውን የአፈና እርምጃ እናውግዝ

ሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም. ወያኔ በአንዋር መስጊድ ምዕመናን ላይ የወሰደው ዘግናኝ የአፈና እርምጃ የዚህን አገዛዝ ጸረ ኢትዮጵያዊነት፤ ጸረ ሕዝብነት፤ ስነ ምግባር አልባነትና ባለጌነት ከመቸውም ጊዜ ባልተናናሰ አጋልጦታል። ወያኔ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ለመብታቸው ያደረጉትንና እያደረጉ ያሉትን ሰላማዊና ፍትሐዊ ትግል ላለፉት ሁለት ዓመታት ማፈን ስላቃተው በቀቢጸ ተስፋ የሕዝብን ተቃውሞ በአረመኔያው ጭፍጨፋ ለማፈን ሲፍጨረጨር በተደጋጋሚ ታይቷል።

ወያኔ የራሱን ቅጥረኛ ተንኳሾች ወደ መስጊዱ ቅጽር አስገብቶ ፖሊሶች ድንጋይ ተወረወረባቸው በሚል ሽፋን ባዘጋጀው ኃይል አማካይነት በሙስሊሙ ዜጋ ላይ ወረራ አካሂዶ የፈጸመው ኢ ሰብአዊ ድብደባ ይህ ነው የማይባል ለመሆኑ ብዙዎች መስክረዋል ። ታላቁ አንዋር መስጊድንም በወታደር ከቦ በበርካታ የጭነት መኪና የተደበደቡና የተንገላቱ በጾም ላይ የነበሩ ዜጎችን አፍሶ ወስዷል ። ወደ ተልየያዩ ማጎሪያዎች ወስዶ የማፍጠርንም (ጾም የመፍታትንም) ዕድል ከልክሎ ከእኩለ ሊሊት በኋላ በከተማው ለጅብ ለቋቸዋል ። አረመኔው ወያኔ የአማኞችን ና የመስጊዱን ሃይማኖታዊ አልባሳቶቻቸውን ገፈውና ቀደው ሲጥሉ በተለይ በሙስሊም እህቶቻችን ላይ ያሳዩት ብልግናና ያዘነቡት ስድብ ሰቅጣጭ ሆኖ ለብዙ ጊዜም የሚታወስ ነው ። የወገኖችን ትግል የመብት ሳይሆን የሃይማኖቶች ልዩነትን መሰረት ያደረገ ወይም የሃይማኖት ጠብ ነው ብሎ ለማሳመን ሲጥር የነበረው ወያኔ በመስጊዱ የነበሩትን ሙስሊሞች ይህ የክርስቲያን ሀገር ነው ወደ ሳውዲ አረቢያ ሂዱ ወዘተ... እያለ የጥላቻ መርዝን ሊያሰራጭ ሞክሯል። ሀፍረት ለወያኔ ባዳ ነው።

የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ትግል በቀጣይነቱ መታየቱ ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ አበረታች ነው ። ለጽናት ምሳሌ ነው ። ትንኮሳና ወያኔያው ሴራን ከማክሸፍ ረገድም ምሳሌ ሊሆን የሚገባው ነው ። በአንጻሩ ሌላው ዜጋ መፋዘዝ ብቻ ሳይሆን ለወያኔም ከፋፋይ ቅስቀሳ ጆሮ ሰጥቶ አልባሌና የተሳሳተ ድምዳሚ ላይ እየደረሰም ነው ። ይህ በአስቸኳይ መቆም ያለበት ነው ። ዜጎች በሞላ ከሙስሊም ዜጎች--ወገኖች ጎን መቆም በጋራ መታገል አለባቸው። የታሰሩትና የተወገሩት ሙስሊሞች ሊሎች ከጎናቸው እየቆሙና እየታገሉ መሆናቸውን በገቢር ማወቅ ይገባቸዋል ። በመሆኑም የጋራ ትግልና ትብብር እንዲኖር ኢሕ አፓ ጥሪውን ዳግም ያስተላልፋል። የሙስሊም ወግኖቻችንን ትግል ይደግፋል፤ ባለው አቅምም ከጎናቸው ይቆማል። ክርስቲያኖችና ዲሞክራቶች፤ ቀሳውስቶችና አባዎች ወዘተ... የሙስሊም ወገኖቻችን ትግል የእነሱም ነውና ድጋፋቸውን እንዲሰጡ፤ ወደ ትግሉ መስክም ደፍረው እንዲገቡ ኢሕአፓ ያሳስባል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ መብቱን ያስከብራል፤ ድልን ይቀዳጃል።

EPRP
PO BOX 73337
Washington, DC. 200056
USA
TEL: (202) 291 4217
Fax: (202) 291 7645

Email: ESPIC@aol.com
Website: WWW.EPRP.com

EPRP
BP 30022
92276 Bois Colombes Cedex
France





Orion Zemene
***VILLA FRESH ITALIAN KITCHEN***
611 Grat Mall DR. FC 11
Milpitas CA 95035
Work 408-946– 8382
Cell 415 –845-7000
Email– Villafikmilpitas@yahoo.com